# የይቅርታ፣ ገደብና አመክሮ አፈፃፀምና የክትትል ስርዓት

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ዚያድ ረድዋን፣

ታደለ ተካ

1. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 199(2) መሰረት የጠባይ መሻሻል ጥበቃ ኃላፊዎች እና የኮሚሽኖች አቋምና ተግባር በሚወጣ ህግ ይወሰናል እንዲሁም የጥበቃ ባልደረባነትን የስራ አፈፃፀም ዝርዝር ስለቅጣት አፈፃፀምና ጉዳዩን በሚመለከት ህግ ይወሰናል ተብሎ በህጉ አንቀጽ 209 (2) በግልፅ ቢቀመጥም እስካሁን ተግባራዊ አልተደረገም፡፡
2. የወንጀል ፍትህ ፖሊሲው የእስር ቅጣት አማራጭ ስልቶችን በተመለከተ የማረሚያ ቤት አስተዳደር በበላይነት ህጎችንና መመሪያዎችን ሊያወጣ እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ ነገር ግን ይህን ተከትሎም የወጣ ወይም የተሻሻለ ህግ የለም፡፡ በመሆኑም የፍርድ ቤት ትእዛዝን ውጤት ፤የጥፋተኛውን የባህሪ ለውጥ፤ህገ ወጥ ተግባሮችንና የደንብ ጥሰቶችን ለማወቅ፤ፍትሀዊ የቅጣት አወሳሰን ለመተግበር የሚያስችል የመረጃ ስርዓት የለም፡፡
3. በሀገራችን የተዘረጋ የጥፋተኞች ቁጥጥርን ስርአት ባለመኖሩ ወይም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 199(2) መሰረት የጠባይ ማሻሻያና ጥበቃ ኮሚሽንም (probation commission) አለመቋቋሙ ዳኞች የቅድመ ማጣራት ተግባር እንዳያዙ እንቅፋት ከመሆኑም በተጨማሪ ይህንኑ መረጃ ከሌሎች ምንጮች ማግኘት አስቻጋሪ በመሆኑ ፍትሀዊ ውሳኔ ለመስጠት ያዳግታል፡፡
4. በማህበረሰቡ በተለያየ ስልት ተለቀው ያሉ ወንጀል አድራጊዎችን የሚቆጣጠር አካል ባለመኖሩ ጥፋተኛውን ከእስር ነጻ ማድረጉ በህግ የበላይነትና ፍትሀዊ የቅጣት አወሳሰን ላይ የተዛባ ምስል በመፍጠር ዜጎች በዳኝነት አካሉ ላይ ያላቸውን እምነት ያሳጣል፡፡ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ጥፋተኛው የጠባይ አመራር ደንቦችን መተግበሩ፤ የባህሪ ለውጥ ማምጣቱንና ሌሎች የህግ ታሳቢ ዓላማዎችን ማሳካቱን ለማወቅ አይቻልም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤት ቅጣትን በመገደብ የተወሰነ የተፈና ጊዜ መስጠት፤አመክሮን፤ገደብና ሌሎች አማራጭ የእስራት ስልቶችን ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ ቁጥጥር የሚያደርግ አካል በማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ አካል ለፍ/ቤት፤ ለአቃቤ ህግ፤

ለፖሊስ፤ ለማረሚያ ቤትና ሌሎች ፍትህ አካላት ወቅታዊ የመረጃ ግብአት በመሰጠት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባዋል።

5 የወንጀል አድራጊዎች የቁጥጥር፤ ድጋፍና የመረጃ ተቋም መመስረት ወሳኝነት የወንጀል ፍትህ ስርአት ከሚጀምርበት ከምርመራ ጀምሮ እስከ ቅጣት አፈፃፀም ያለውን የአንድ ወንጀል አድራጊ ታሪክና መረጃ ግልፅ፤ በተደራጀና ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ በማዋቀር የክትትሉን ህጋዊ ውጤቶችን ለወንጀል መከላከል ተግባርና ለፍትህ ስኬት ለመጠቀም ያስችላል፡፡

6 በብዙ አገሮች የጥፋተኞች ቁጥጥርን በተመለከተ በበላይነት የማደራጀትና የመቆጣጠር ሥልጣን የሚሰጠው ለአገሩ የፍትህ ሚንስቴር ነው።ይችላል የሚል ስጋት አይኖርም። ምክንያቱም ዓቃቤ ህግ ህዝብና መንግስትን ወክሎ በማስረጃ ላይ በመመስረት በጥፋተኞች ላይ የሚገባቸውን ቅጣት የማስወሰን ሀላፊት አለበት። ስለዚህ ፍትህ ሚኔስትር በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥፋተኞችን በተቀመጠላቸው ቅድመ ሁኔታ ገለልተኛ በሆነ መልኩ የማስጸም አቅም ይኖረዋል፡፡ ፍርድ ቤት የተለያዪ የማህበራዊ ማረም ስልቶችን ሊወስን ይችላል አሊያም በሀገራችን የወንጀል ፖሊሲ መሰረት የህዝብና የመንግስት ጥቅም የሚጎዱ ጉዳዮች ካልሆኑ በስተቀር ተጨባጭ ማስረጃ ተገኝቶም አቃቤ ህግ የተለያዪ አማራጭ እርምጃዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚችል በወንጀል ፍትህ ፖሊሲ አስቀምጧል፡፡ ስለዚህ ከሳሹ አካል ሁሌም ቢሆን ጥፋተኞችን ወደ ማረሚያ የማስገባት አላማ ብቻ እንዳለው አድርጎ መሳል ተገቢ አይደለም። ከላይ እንደተጠቀሰው ተገቢውን ጥፋተኛ ገና ከክስ ሂደት ጀምሮ በመለየት በህብረተሰቡ ውስጥ ሆኖ ቁጥጥር እየተደረገበት ሊቀጣና በዚህ ሂደትም አቃቤ ህግ ከየትኛውም የፍትህ አካል በተሻለ መልኩ ለውጤታማ አተገባበር ከፍተኛ ሚና አለው። በብዙ ሀገሮች የማረሚያ ቤቱ ተጠሪነት ለፍትህ ሚኒስትር በመሆኑ በህብረተሰብ ውስጥ ተለቀው ያሉ ጥፋተኞችን መከታተል ከተለመደው የማረሚያ ቤት የታራሚዎች አያያዝ በጣም የሚለይ በመሆኑና

የራሱ አዲስ የሆነ ፅንሰ ሃሣብ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ በፌዴራል ፍትህ ሚኒስትርና በክልል መንግስት ስር ባሉ የፍትህ ቢሮዎች በኩል የቁጥጥር ተግባር ቢደራጇ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡

7 የሚቋቋመው የጥፋተኞች ቁጥጥር አካል ከፍተኛ ጊዜና ወጪ የሚይጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰራተኞችን በምደባና በዝውውር፤የቢሮ ቁሳቁሶችን በማራሚያ ቤት አካባቢ ከሚሰሩ ድርጅቶች በእርዳታ፤ከጥፋተኞች ከሚሰበሰብ ክፍያና ከመንግስት ከሚገኝ በጀት በማውጣጣት መፍትሄ ሊገኝለት ይችላል፡፡ በመሆኑም እንደ አጥኚዎቹ እምነት በፍትህ ሚኒስትር ስር የሆነ አካል በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥፋተኞችን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ስልጣን ተሰጥቶት ቢቋቋም ተመራጭ ነው፡፡

8 ከዚህ ጋር በተያያዘ በተጨማሪ እንደ ተጓዳኝ አደረጃጀት በአንዳንድ ሃገሮች የይቅርታ፤የተወሰነ የፈተና ግዜና አመክሮ ቦርድ በፍትህ ሚኒስቴር ስር የሚገኝና የጥፋተኞችን ቁጥጥር በተመለከተ የፖሊሲ ጉዳዮችና መመሪያዎችን በማውጣት ቁጥጥርና ጥሰቶች ሲገኙ የመሻር ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት የተሰጠው አካል አለ፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ወቅት የፍትህ ሚኒስቴር አንድ አካል የሆነው የይቅርታ ቦርድ ጽ/ቤት ይቅርታ የማድረግና የመሻር የውሣኔ ሃሣብ ለኘሬዝዳንቱ የማቅረብ ስልጣን የተሰጠው እንደመሆኑ ቦርዱን እንደገና በማደራጀት የተለያዩ አማራጭ የቅጣት ስልቶች የሚተገበሩበት የስትራቴጂና የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥና ታራሚዎች በተለያዩ የመልቀቂያ ዘዴዎች ከማረሚያ ቤት የሚለቀቁበትንና የቅጣት ቅናሽ የሚያገኙበትን ስርአት የመዘርጋትና የማህበራዊ ማረም ትእዛዞችን የመሻር፣ ከእያንዳንዱ ጥፋተኛ አንጻር የቁጥጥር ደረጃና ጊዜ የመወሰን ስልጣን እንዲኖረው ማድረግ እንደ ንኡስ አማራጭ መያዙም ተገቢ ነው፡፡

9 በጥፋተኞች ቁጥጥር ስርአት ውስጥ ዋነኛ ተዋናዮቹ የጥበቃ ባልደረቦች ናቸው፡፡ የጥበቃ ባልደረባነት ማለት የማህበረሰባዊ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ፍሬ እንዲያስገኙ በመንግስት የበላይ

ተቆጣጣሪነት ለዚሁ ተግባር በተቋቋሙ መንግስታዊ ወይም ግላዊ ባህሪይ ባላቸው ማህበራት ወይም ቡድኖች ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት ነው፡፡ የጥበቃ ባልደረባ ዋና ተግባር ጥፋተኞች ቅጣታቸው በተገደበላቸው ጊዜም ሆኖ በአመክሮ ወይም ቅጣታቸውን ፈፅመው ከተፈቱ በኋላ ማህበራዊ ኑሮ እንደገና እንዲለምዱ፤ ወደ ደንበኛ ማህበራዊ ኑሮ እንዲመለሱና ደጋግመው ወንጀል እንዳያደርጉ ምክር መስጠት፤ ወደ ቀና መንገድ መጥራትና የመልካም ጠባይ እና ሌሎችን እርዳታን ማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪ የጥበቃ ባልደረባነት ስልጣን የተሰጠው ድርጅት በተቻለ መጠን ተጠባባቂዎቹን በስራ ላይ ሊያውላቸው፤ስራ ሊሰጣቸው፤ስራ ወይም መኖሪያ ወይም እርዳታ እንዲያኝ ሊያግዛቸው ወይም በስራቸው የሚያገኙትን ደመወዝና ጥቅም ለተገቢ ጉዳያቸው እንዲያውሉትና በጠቅላላውም በደንበኛው ማህበራዊ ኑሮ ለመኖር የሚችሉበትን ማናቸውንም ድጋፍና እርዳታ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ዘውትር በግልጽና በስውር ቁጥጥር በማድረግ ሪፖርት ለፍ/ቤትና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባሉ፡፡ የጥበቃ ባልደረባነት በመንግስት ቁጥጥር ስር በሆነ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ወይም በየጊዜው ለሚመረጥ ጠባዪ ለፈተናና ለዚሁ ኃላፊነት ብቁ ለሆነ ግለሰብም ሊሰጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ለፖሊሲ መስሪያ ቤት ስራውን በሌላ ሁኔታ ለማካሄድ እስከተቻለ ድረስ አይሰጥም፡፡ የጥፋተኞች ቁጥጥር ስርአት ፍ/ቤት የሚወስነውን ደንቦች በፈተና ጊዜው ውስጥ በትክክል መተግበሩን መከታተያ ስልት ነው፡፡ የጥፋተኞች ቁጥጥር ስርዓት ፍ/ቤት በሚወስነው ደንቦች መሰረት ይተገበራል፡፡ ምክንያቱም ደንቦቹ የወንጀል አድርጊውን ለመቆጣጠር፤የባህሪ ለውጥና ተሃድሶ ለመከታተል ያለሙ፤ህብረተሰብን ከተጨማሪ አደጋና ወንጀል ለመከላከልና ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ በመሆኑም ይህን ተግባራዊ ለማድረግ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በማረም ሂደት ውስጥ ጠቃሚ የስርአተ ትምህርት ፕሮገራሞችን በመቅረጽ ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡

10 ውጤታማ የጥፋተኞች ቁጥጥር ስርዓት ለመዘርጋት ወጥ የሆነ የቁጥጥር ደረጃዎች/መጠን (Degree/category) ማውጣት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሚወሰነው ወንጀል አድራጊው በህብረተሰቡ ላይ ከሚያደርሰው አደጋ (Risk to community) አንፃር ነው፡፡ ከባድ አደጋና ስጋት የሚሆኑ ጥፋተኞች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግና ምንም አደጋ የማይፈጥሩትን በተመለከተ ደግሞ ቀለል ያለ ቁጥጥር መጠቀም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እንደ ጥፋተኛው ለውጥና ትብብር የቁጥጥር ደረጃዎች (Degrees of supervision) እየለሉና ጥፋተኛውን ነፃ ወደ ማድረግ ሁኔታ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ በዚህ መሰረት እነዚህ ደረጃዎች ከከፍተኛ ጥብቅ ቁጥጥር እንደ ወንጀል አድራጊው የባህሪ ለውጥና በጎ ትብብር ወደ ዝቅተኛ ቁጥጥር እየወረደ ሊመጣ ወይም በተቃራኒው ከዝቅተኛ ቁጥጥር ወደ ከፍተኛ እንደ ሁኔታው ሊሸጋገር ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት የቁጥጥር ደረጃዎችን በአራት ምድብ መክፈሉ ተገቢ ነው፡፡ እነዚህም ያለ ቁጥጥር (No Supervision) (ይህ ማለት ጥፋተኛው ቢያንስ ለጽ/ቤት በወር አንዴ ወይም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሪፖርት የሚያደርግበት ነው)፤አነስተኛ ቁጥጥር (Minimum Supervision) (ይህ እንደ ሁኔታው ለጥፋተኛው ምንም ቅድሚያ የማሳወቅ ተግባር ሳይኖር በቤቱ ጉብኝት በወር ሁለቴ የሚደረግበት ነው)፤መካከለኛ ቁጥጥር (Medium Supervision) (በዚህኛው ደረጃ የቤት ውስጥ እስር (House Arrest) እና በሳምንት የቤት ጉብኝት ይደረጋል)፤ከፍተኛ የሆነ ቁጥጥር (Maximum Supervision) (ከሁለት እስከ ሦስት ጊዜ በሳምንት በጥፋተኛው ስራ ቦታ አሊያም መኖሪያ ቤት ጉብኝት የሚደረግበት፣ የቤት እስር፣ የኤሌክትሮኒክ ቁጥጥር፣ የተሰረቁ እቃዎችንና አደንዛዥ እፅ ያለመበርበሪያ ትዕዛዝ በፖሊሲ ኃይል የሚበረበሩበት የጥብቅ ቁጥጥር ደረጃ ስርአት ነው)፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤት በፈተና ግዜ አሊም በሌላ ስልቶች ወደ ህብረተሰቡ ጥፋተኛው እንዲለቀቅ ሲይዝ የሚቋቋመው አካል ሊደረግ የሚገባውን የቁጥጥር ደረጃ በዚህ መልኩ ተግባራዊ ማደረግ አለበት፡፡

11 በጥፋተኞች ላይ የቁጥጥር ደረጃና ስልቶችን በተመለከተ መተግበር ያለበት አሃዛዊ ወይም መዋቅራዊ ቅርፅ ያለው (quantitative Decision Making system or structured model) የውሣኔ አሰጣጥ ስርአት ነው፡፡ ይህ ሞዴል በአብዛኛው ሃገሮች የሚተገበር ሲሆን በውሣኔ አሰጣጥ ሂደት የወንጀሉን ክብደት፤ የስጋት ግምት ፤የጥሰት ደረጃዎችን ፤የቅጣቱ ክብደትና የስውር ቁጥጥር ደረጃዎችን እንደመመዘኛ ይጠቀማል፡፡ በመሆኑም የሚዋቀረው የጥፋተኞች ቁጥጥር አድራጊ አካል የእያንዳንዱን ጥፋተኛ ግላዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ አሃዛዊ የውሣኔ የአሰጣጥ ስርአትን (Quantified Decision – Making tools) ከውሣኔ አሰጣጥ ጀምሮ እስከ ትዕዛዙ መሻር ባለው ሂደት ተግባራዊ በማድረግ አድሏዊ አሳራርን ማስወገድ ይኖርበታል፡፡ አሃዛዊ የውሣኔ አሰጣጥ ሲባል በቁጥር ላይ የተመሰረተ ነው ለማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም የአደገኛነት ሁኔታ፤ የወንጀል ክብደትና የተወሰነው ቅጣት ክብደት ከተጠና በኋላ የሚወጣ ደረጃን ለማመላከት ብቻ ነው፡፡ ይህ አሃዛዊ የውሣኔ አሰጣጥ ስልት በራስ የመወሰን ሰፊ ስልጣንን(discretion) ለማጥበብና ወጥ የሆነ የጥፋተኞች ቁጥጥር በፈፃሚ ባለሙያዎች እንዲተገበር ይረዳል፡፡ በተጨማሪ ለውሣኔ አሰጣጥ ሂደት የስጋት ወይም የአስፈላጊነት መላምት መሳሪያዎችን (risk need prediction instruments) ተግባራዊ በማድረግ ያለውን የሰው ሃይልና የገንዘብ ፍሰት ወደ አደገኛና ለህብረተሰብ ስጋት ወደ ሆኑ ጥፋተኞች ማተኮር ይቻላል፡፡እንዲሁም በመዋቅራዊ መመሪያ የተመሰረተ የተወሰነ የፈተና ጊዜና ሌሎች የማህበራዊ ማረም ስልቶችን ትዕዛዝን የመሻር ስትራቴጂ (Stuctursd revocation strategy) መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የጥሰቱን ክብደት በመመዘን የቁጥጥር ጊዜውን ማራዘም፤ ማሻሻል አሊያም የተወሰነ የፈተና ጊዜ ትዕዛዙን በመሻር ወደ ማረሚያ ቤት መላክ ሊሆን ይችላል፡፡ የተቀመጡ ደንቦችን መጣስ የሚያስከትለው ውጤት ግልፅ የሆነ የስጋት አመልካቾችን (Risk prediction) በመጠቀም ሊሆን ይገባል፡፡ ለምሳሌ የተወሰነ የፈተና ጊዜ ደንቦችን ጥሰትን በተመለከተ

እየጨመረ የሚመጣ (Scheme of escalating sanctions program) የቁጥጥር ደረጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ እያንዳንዱ ጥሰት ለምሣሌ መጠጥ መጠጣት ወይም በቀጠሮ ሰአት ያለመገኘት በቀጥታ ትዕዛዙን ከማሻር ይልቅ ጠበቅ ያለ የቁጥጥር ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን፤ መካከለኛ ቅጣቶች (intermediate sanctions) ማለትም እንደ የቤት እስር፤ የተወሰነ የፈተና ጊዜ ማቆያ ጣቢያና (probation detention centre) የፀባይ ማረሚያ ማዕከል በመጠቀም በተቻለ መጠን ጥፋተኛውን ከማረሚያ ቤት ለማራቅ ይሞክራሉ፡፡ስለዚህ የሚቋቋመው የጥፋተኞች ቁጥጥር አድራጊ አካል በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ይህን የውሳኔ አሰጣት ስርአት ሊከተል ይገባዋል፡፡

12 በጥፋተኞች የክትትል ስርአት ውስጥ ወቅታዊ የሆነ የውይይት ፎረም በማዘጋጀት ህብረተሰብን በማረም ሂደት ውስጥ አሳታፊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የእነዚህ ፎረሞች ዋና አላማ በጥፋተኞች መቆጣጠር ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍትሄ ለመስጠት፣ ከጽ/ቤቱ ስራ ጋር ህብረተሰቡን ለማስተዋወቅና የፖሊሲ ማሻሻያ ሃሣቦችን ለማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም የጥፋተኞች ቁጥጥር ስርአት በመዘርጋት ሂደት የህዝብ አስተያየት ከግምት መግባት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ህብረተሰብ ምንም እንኳን ያጠፋ የወንጀል አድራጊ በደንብ እንዲቀጣ ቢፈልጉም የተወሰነ የፈተና ጊዜና ሌሎች ማህበራዊ ማረም ፕሮግራሞች አስፈላጊነት በማስረዳት፤ የወንጀል መከላከል ተግባርን እንዴት ውጤታማ እንደሚያደርግ በማብራራት ስርአቱ ጥሩ ገፅታ እንዲኖረው ማድረግ ይቻላል፡፡

13 የጥፋተኖች ክትትል ላይ ከፍተኛ ድርሻ እያበረከቱ የሚገኙት በጎ ፈቃደኞችና ህዝባዊ ኮሚቴዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የወንጀል ሰለባዎችንና ቤተሰቦቻቸውን በመርዳትና ጥፋተኛው ወደ ህብረተሰቡ የሚቀላቀሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት በአጥፊዎችና በህብረተሰቡ መካከል የተሻለ ግንኙነት ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡ በጎ ፈቃደኞችና ህዝባዊ ኮሚቴዎች በትምህርት፤በማህበራዊና በእምነት ነክ አገልግሎቶችን ለጥፋተኞች

በመስጠት ይሳታፋሉ፡፡ ይህን በማድረግ በማረም ስርአቱ የህብረተሰቡ ምክርንና ድጋፋ መሰብሰብ ይቻላል፡፡ በተጨማሪ ጽ/ቤቱ በሚገኝበት ሁሉም አካባቢዎች ብዙሃኑን የፍትህ አካላትን ያካተተ የተቀናጀ የህዝብ ደህንነት ስርዓት( MAPPA-Multi Agency public protection Arrangements) በመዘርጋት ጽ/ቤቱና የተለያዩ መ/ቤቶች የመረጃ ልውውጥ እንዲያደርጉ፤እንዲተባበሩ በማድረግ ወንጀል አድራጊዎች አደገኛና ህገ ወጥ ተግባር እንዳይፈጽሙ በመከላከል የህዝብን ደህንነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

14 እንዲሁም የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ (Community Policing) ፅንሰ ሃሳብን ማለትም የፖሊስ ኦፊሰሮች በእያንዳንድ አካባቢ በመመደብ ከህብረተሰብ ጋር ጥሩ መቀራረብና ትውውቅ እንዲኖራቸው ማድረግ የሚለውን መርህ በማህበራዊ ማረምና በተወሰነ የፈተና ጊዜም ተገባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡

15 በህብረተሰቡ ጥሩ እውቀትና ተቀባይነት ያላቸውን የጥበቃ ባልደረቦች በማሳተፍ የጥፋተኛውን ቁጥጥር በተሻለ ደረጃ ላይ ማድረስ ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ ስለ እያንዳንዱ ጥፋተኛ ለህብረተሰብ በማሳወቅ በቁጥጥር ሂደቱ ተሳታፊ ማድረግ ይቻላል፡፡

16 የማህበራዊ ማረም ሀላፊት የተሰጠው ተቋም አሊያም የጥፋተኞች ቁጥጥር የሚያደርገው አካል የፖሊስ የጋራ ትብብር /Probation-Police cooperative Action/መመስረት ይኖርበታል፡፡ ይህ የጥበቃ ባልደረቦች ከህግ አስከባሪ አካሎች ጋር በቅርበት እንዲሰሩና በቁጥጥሩ ሂደት ስለ እያንዳንዱ ጥፋተኛ መረጃ እንዲለዋወጡ ይፈቅዳል፡፡ እንዲሁም ፖሊስ በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ደንብ እንዲያውቅ ይደረጋል፡፡

17 የወንጀል መከላከል ተግባር የበለጠ ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ቤት-የማህበራዊ አገልግሎት-ፖሊሲ (School-social service-police-SSP) የጋራ እንቅስቃሴ በየአካባቢው መመስረት ይኖርበታል፡፡እንዲሁም የዜጎች አማካሪ ኮሚቴ (citzen Advisory committees) በተጓዳኝ ማዋቀር ያስፈልጋል፡፡

18 በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥፋተኞችን በምን አይነት የቁጥጥር ስልት ነው ልንከታተል የምንችለው የሚለው ጥያቄ የሚመለሰው ምን አይነት አደረጃጀት መዘርጋት አለበት በሚለው ጥያቄ ውስጥ ነው፡፡

ለዚህም በቅድሚያ የጥፋተኞች ቁጥጥር አድራጊ አካል በፍትህ ሚኒስትር ስር እንዲደራጅ ማድረግ። በመቀጠል በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥፋተኞችን እንዴት አድርገን መቆጣጠር እንችላለን የሚለውን ጥያቄ የኤሌክትሮኒክ የቁጥጥር መንገዶችን (Electronic Monitoring)፤የሪፖርት ጣቢያዎች (Reporting kiosks)፤በርቀት የአደንዛዥ እፅ መጠቀም መፈተሻ መሳሪያዎች (Remote substance use detection devices)፤ጥፋተኛው የተወሰኑ ደንቦችን እየተገበረ መሆኑን መከታተያ መሳሪያ(Monitoring equipment to detect offender's compliance with Restrictions)፤የጥፋተኛውን እንቅስቃሴ አመላካች መሳሪያ (Track offenders locations)፤የቤት እስር (Home Monitoring)፤ድብቅ ቁጥጥር (Surveillanc)፤ በቤትና በቢሮ የስልክ ጥሪ ማድረግ (Phono call to – Home & office)፤ የመኖሪያና የስራ ቦታን በተወሰነ ጊዜ ጉብኝት ማድረግ፤ከተወሰነቦታ/አካባቢ ውጭ ያለፈቃድ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ ፤በማህበራዊ አገልግሎት እዲሰጥና በማቆያና የካሳ ማእከላ (restitution center) የሚሉትንና ሌሎችን እንደ ሀገራችን ነባራዊ ሁኔታና የኢኮኖሚ አቅም በዘመኑ ካሉት የቴክኖሎጂ ግኝቶችና በጥፋተኞች ቁጥጥር በዘርፉ ከላቁ ሀገሮች ተሞክሮ በመነሳት ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል።

19 በሀገራችን ያሉትን የማህበራዊ ማረም/ከእስር ውጭ ያሉ ስልቶችንና የአፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታና ሞዴል በደንብና በመመሪያ ማውጣትና ነባሮችን የማሻሻል ስራ ያስፈልጋል። እነዚህ ህጎች ቅጣትን በመገደብ የተወሰነ የፈተና ግዜ መስጠት፤ አመክሮ፤ ይቅርታ፤ የማህበራዊ አገልግሎት፤ ከማረሚያ ቤት የሚሰጡ የተለያዩ ፈቃዶች፤ የጥንቃቄ እርምጃዎች፤ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ፤ የገንዘብ መቀጮና ሌሎች ከእስር ውጪ ያሉ አማራጭ ስልቶችን ይመለከታል። እነዚህ ስልቶች ለፍርድ ቤቶችና ለማረሚያ አስተዳደርና ለቁጥጥር አድራጊ አካሉ የተለያዩ የመፍቻ/የመልቀቂያና የትእዛዙን የመሻር ስልጣን በመስጠት ስልቶችን የበለጠ ተግባራዊ የሚደረጉበትን አግባብና ሀላፊት ይዘረጋል።

20 በይቅርታ የሚለቀቁ ጥፋተኞችን በተመለከተ ከሌሎቹ የማህበራዊ ማረም ስልቶች ልዩ የሚያደርገው ሁኔታዎች ቢኖሩም ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ አሊያም ከጥፋተኛው ሁኔታ የተነሳ ቁጥጥር አስገዳጅ ከሆነ ልክ እንደ ገደብና አመክሮ የቁጥጥር ስርአት በመቁጠር ዝርዝር ሁኔታውን በህግ በመደንገግ ሊፈጸም ይችላል፡፡

21 በወንጀል ህጉ ለተቀመጠው የተወሰነ የፈተና ግዜ ስርአት የቀጭነት ባህሪ (Punitive) ድግሪውን ከፍ ለማድረግ እንዲረዳ በአንዳንድ ሀገሮች የሚተገበረውን ጥብቅ የሆነ የተወሰነ የፈተና ጊዜ ቁጥጥርን (Intensive Supervision Probation) ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ አማካይ የሆነ ትእዛዝ ከተለመደው የተሀድሶ እሳቤ ወጣ በማለት ጥፋተኛውን ጥብቅ በሆነ የቁጥጥር ደረጃ እንዲተገበርበት ይፈቅዳል፡፡ በመሆኑም ከእስራት ቅጣት ያነሰ ነገር ግን ከተለመደው የገደብ ትእዛዝ የከበደ ውሳኔ በጥፋተኞች ላይ መወሰን ሲያስፈልግ ይህ ስልት መጠቀም ይገባል፡፡

22 ፍ/ቤቶች ለአጠባበቅና ለቁጥጥር የሚረዱ ደንቦችን እንደው በጥቅሉ በመልካም ጠባይና ከህገ ወጥ ተግባር እንዲታቀብ በሚል ከማስቀመጥ የወንጀል አድራጊውን የባህሪ ለውጥ የሚያመጡና የህብረተሰቡን ደህንነት የሚያረጋግጡ ዝርዝር ደንቦችን ሊወስኑ ይገባል፡፡ እንዲሁም የደንቦችን የበለጠ ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የተወሰነ የፈተና ጊዜና ሎሎች የማህበራዊ ማረም ቅጣቶች ተወስኖባቸው የሚመጡ ጥፋተኞችን በተዋቀረው የጥፋተኞች ቁጥጥር አካል ለተወሰነ ቀናት ገለፃ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪ ጥፋተኞች ደንቦችን በቅጡ እንዲገባቸው በማስቻልና የጥሰት ውጤት ምን እንደሆነ የሚያብራራ መመሪያ የያዘ መፅሐፍ መስጠት፣ የማህበራዊ አገልግሎት ቢያንስ በሳምንት አንዴ እንዲሰጡ በማድረግ የጽ/ቤቱን ጠንካራ አቋም በማሳየትና በማሳመን ጥፋተኞችን ለለውጥ የማዘጋጀት ተፅኖ ይኖረዋል፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ የጠባይ አመራር ደንቦች ሊተገበሩ የሚችሉ፤ ህጋዊ፤ ሞራላዊና የጥፋተኛውን የተሀድሶ ሂደት የሚያጠናክሩና የወንጀል ደጋጋሚነትን የሚቀንሱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

23 እንዲሁም ለማህበራዊ ሰራተኞችና በማረም ዘርፍ ላሉ ባለሙያዎች በህብረተሰቡ ውስጥ የቅጣት አተገባበር መከታተያ ዝርዝር ህጎችና መመሪያ በማዘጋጀት፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በመስጠት ደንቦቹን በተሻለ ሁኔታ ማስፈጸም ይቻላል። ስለዚህ በወንጀል ሕጉ ላይ የተቀመጡትን የጠባይ አመራር ደንቦችን በማካተትና በማጎልበት እንደ ወንጀሉ አይነት የደንብ አፈጻጸም መመሪያ በመስጠት ጥፋተኛው በግልፅ ሊያደርግ/ሊቆጠብ የሚገባውን ነገር እንዲገነዘብና እራሱን በዚሁ መሰረት በመምራት ህግ አክባሪ ዜጋ በመሆን የህብረተሰቡን ደህንነት ከሚያናጉ ተግባራት እራሱን እንዲያርቅ ይረዳል።

24 የማህበራዊ ማረምና የተወሰነ የፈተና ጊዜን ለህብረተሰብ ለማስተዋወቅና በጎ ገፅታ ለመገንባት አዲስ የመጡ ጥፋተኞችንና የተወሰነባቸውን ደንቦችን የጣሱትን አንድ ላይ በማድረግ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ይገባል። ለምሣሌ መንገድ እንዲያፀዱና የማዘጋጃ አረንጓዴ ቦታዎችን እንዲንከባከቡ ሊደረግ ይችላል። የማህበራዊ ማረምና የተወሰነ የፈተና ጊዜን ጥሰቶችን በቅጣት እርምጃ ብቻ ሳይሆን የባህሪ ለውጥና የመነሳሳት ሁኔታን ለመፍጠር አንዳንድ የማበረታቻ ተግባሮችንም እንደ እርምጃ መውሰድ ይቻላል። ይህም የፈተና ጊዜውን/ቁጥጥር ግዜውን በአግባቡ እንደተወጣ መግልጽና የመልካም ባህሪ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት፣የቁጥጥር ደረጃውን ላላ በማድረግ መቀነስ ለምሳሌ የጉዞ ነፃነቱን በሳምንቱ መጨረሻ መስጠት፣የቤት እስር ሁኔታውን ላላ ማድረግ ይህ ለአደገኛ ጥፋተኞች ቢሆንም ይቻላል፣የፈተና ጊዜውን ማሳጠር ወይም መቀነስ የሚሉትን ሊሆን ይችላል።

25 ሀገር አቀፍ የጥፋተኞች የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት እንዲኖር በፌዴራልና በክልል መንግስት መካከል ግልጽ የሆነ የትብብር መንገዶችን በህግ በማስቀመጥ ታራሚው ከአንዱ ክልል ወደ ሌላ ክልል ሲዘዋወር የክትትል ተግባሩም አብሮ ለሚመለከተው ክልል የሚተላለፍበት ስርአት ሊዘረጋ ይገባል። ክልሎችም የራሳቸውን የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት የፌዴራሉን አወቃቀርና የአካባቢውን ሁኔታ መሰረት በማድረግ ሊዘረጉ ይችላሉ።

በፌዴራልና በክልል መንግስታት መካከል የሚኖረው የስራ ክፍፍል አደረጃጀት፣ ቅንጅት፤ የአፈፃፀም ሞዴልና የቁጥጥር አግባብ የጥፋተኞች ቁጥጥር አድራጊ አካልን ለማቋቋም በሚወጣው ህግ ቢካተት ይመረጣል፡፡

26 የሚቋቋመው የጥፋተኞች ቁጥጥር አድራጊ አካል በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጸሙ የተለያዩ የማረም ስልቶችን ባቀፈ መልኩ ማከናወን ይኖርበታል፡፡ በሀገራችን የወንጀል ህግ የተቀመጡ የቁጥጥር፤ የቅድመ ማጣራት፤ አስተዳደር፤ ድጋፍና ምክር አገልግሎቶችን ተግባራት ጨምሮ የማህበራዊ አገልግሎት፤ የተለያዩ ፈቃዶችንና ሌሎችንም እንደ ሁኔታው በአማራጭ የቅጣት ማስፈጸሚያ ስልቶች ህግና ሌሎች ተመሳሳይ ህጎች ውስጥ የቁጥጥር አድራጊ አካል ስልጣንና ተግባር በማድረግ በተለያዩ ሀገሮች ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን ወጥ የሆነ የጥፋተኞች አስተዳደር (“end to end offender management”) አሰራር በመተግበር ወጥና የተደራጀ ስርአት ለመፍጠር ይቻላል፡፡

27. በሀገራችን የጥፋተኞች ቁጥጥር ስርአት ለመዘርጋት መጀመሪያ በማህበራዊ ማረም ዘርፍ ዙሪያ ያሉ ህጎችን በአግባቡ በመፈተሽ መሻሻል ያለባቸውንና አዲስ ሊወጡ የሚገባቸውን የህግ ማእቀፍ መለየት ያስፈልጋል፡፡ በሀገራችን የወንጀል ህግ፤ህገ መንግስት፤የይቅርታ ስነስርአት አዋጅና የማረሚያ ቤቶች የታራሚዎች አያያዝ ደንብና ማቋቋሚያ ጥፋተኞችን በተለያዩ ስልቶች ወደ ህብረተሰቡ የተወሰነውን ወይም ሙሉውን ቅጣት ቀሪ በማድረግ ለመልቀቅ የሚቻልበትን መሰረታዊ መርሆችና ጠቅላላ ማእቀፍ ተዘርግቷል፡፡ ነገር ግን ጥፋተኛውን በማህበረሰቡ ውስጥ ለመቆጣጠር የሚያስችል አካል ማቋቋሚያ ደንብ፤ የቁጥጥር ጊዜ፤ ደረጃ፤ ስልትና የጥበቃ ባልደረቦችን ስልጣንና ሀላፊነት፤ የተጓዳኝ አደረጃጀቶች መዋቅር፤ በይቅርታ፤ በአመክሮና በገደብ በሚለቀቁ ጥፋተኞች ላይ የሚቀመጡ ደንቦች ዝርዝር አፈጻጸምና የውሳኔ አሰጣጥ መመሪያ፤ የፍትህ አከላት ቅንጅትና የጋራ ማዋቅር፤ የትእዛዝ መሻርና ውጤቱና ሌሎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጥፋተኞች የቁጥጥር ስርአት ለመተግበር የሚረዱ ማእቀፎችን በግልጽ በህግ ሊደነገጉ ይገባል፡፡